# በ4ኛው ብሔራዊ ምርጫ
## የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለምን ሙሉ በሙሉ ተሸነፉ ?

ከስንታየሁ ይመር

የአራተኛው ብሔራዊ ምርጫ በተቃዋሚዎች አጠቃላይ ሽንፈት መጠናቀቁ በሁሉም ተዋናዮች ይሁን ታዛቢዎች ዘንድ የተገመተ አልነበረም፡፡ ሆኖም ውጤቱ በአጋጣሚ የመጣ ሳይሆን የተለያዩ ፖለቲካዊና ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ነበሩት፡፡ ከዚህ አንፃር ምርጫው በእኩል የመወዳደሪያ ሜዳ ላይ እንዲካሄድ የተወሰዱት እርምጃዎችና ለመጨረሻው ውጤት ምክንያት የሆነ ጉዳዮች በአጭሩ እናያለን፡፡

### ሀ. የምርጫ ዝግጅት

መንግሥት ሁሉም ፓርቲዎች እኩል የመወዳደሪያ እድል እንዲኖራቸው፣ ችግሮችም ሲከሰቱ የሚፈቱበትና ምርጫው በአገር ውስጥና በውጭ ታዛቢዎች ፊት በነፃነት እንዲካሄድ ሁኔታዎችን አመቻችቷል፡፡ ከነዚህ ተጨባጭ እርምጃዎች ዋና ዋናዎቹ፡-

1. የምርጫ ቦርድ ምርጫውን በበላይነት የሚመራ እንደመሆኑና በቦርዱ በሁሉም ፓርቲዎች ዘንድ እምነት እንዲኖር አስፈላጊ በመሆኑ በፓርላማ ወንበር ያላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያመኑባቸው የ24 ሰዎች ዝርዝር ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀርበው ከነዚህ 9 ሰዎች ተመርጠዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ሦስቱ በተቃዋሚ ፓርቲዎች በ24ቱ ዝርዝር ውስጥ እንዲገቡ ካደረግዋቸው መካከል ናቸው፡፡ /አውሮፓ ሕብረት የቦርዱ ፕሮፌሽናሊዝም ማድነቁ ልብ ይሏል/

2. መንግሥት ካለው ውሱን አቅም 8 ሚሊዮን ብር መድቦ ለፓርቲዎች የገንዘብ ድጐማ በመስጠት የተወዳዳሪነታቸው አቅም ለማጐልበት ጥረት አድርጓል፡፡ የተመደበው ገንዘብ ለፓርቲዎች የተከፋፈለው ገዥው ፓርቲና ተቃዋሚዎች በተስማሙበት ቀመር ነው፡፡

3. ፓርቲዎች ኘሮግራማቸውን በበቂ ደረጃ እንዲያስተዋውቁ በገንዘብ ሲተመን 38 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የነፃ የቴሌቭዥንና የሬዲዮ የአየር ሰዓትና ነፃ የገዜጣች ዓምድ ሰጥቷል፡፡ /አብዘኛዎቹ ተቃዋሚ

ፓርቲዎች የተሰጣቸው ነፃ የአየር ጊዜና የጋዜጣ አምድ ከ50% በታች እንደተጠቀሙበት ልብ ይሏል/ በፓርቲዎች ምክክር በተደረሰው የክፍፍል ቀመር መሰረት ገዥው ፓርቲ ከጠቅላላው የተመደበው የአየር ሰዓትና አምድ ከ30% ያነሰ ደርሶታል፡፡

4. ሕዝቡ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ምርጫ እንዲያካሂድ 9 ዙር ፓርቲዎች በፖሊሲ አማራጮቻቸው ላይ ክርክር አድርገዋል፡፡

5. ከ65 ፓርቲዎች በላይ የተስማሙበትና በመጨረሻ ሕግ የሆነው የፓርቲዎች ስነምግባር ደንብ ምርጫው በተስተካከለ የጫወታ ሜዳ ላይ በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ እንዲካሄድ አስችሏል፡፡ ሕጉ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀና በአብዛኛው International Institute for Democracy and Electoral Assistance ( IDEA) የተወሰደ ነው፡፡ ፓርቲዎች ቅሬታ ሲኖራቸው የሚፈቱበት የፖለቲካ ፓርቲዎች የምክክር ም/ቤት በየደረጃው ተቋቁሞ ችግሮችን ፈቷል፡፡ በም/ቤቱ አባል መሆን ያልፈለጉ ፓርቲዎች ጉዳያቸውን ወደ ቦርድ አቅርበው መፍትሄ አግኝተዋል፡፡

6. የተቃዋሚ ፓርቲዎች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት የመራጮችና የእጩዎች ምዝገባ ጊዜ ከአንድ ወር በላይ ተራዝሟል፡፡ በዚሁም መሠረት በ1997ቱ ምርጫ ከተመዘገቡት በአምስት ሚሊዮን ከፍ ያለ 32 ሚሊዮን መራጭ የተመዘገበ ሲሆን 63 ፓርቲዎች 2113 ለፌዴራል ተወካዮች ም/ቤት ፣ 4487 ደግሞ ለክልል ም/ቤቶች በእጩነት ተመዝግበዋል፡፡

7. የምርጫ ጣቢያዎች ቁጥር በማብዛት በአንድ ጣቢያ እስከ አንድ ሺህ ሰው ብቻ እንዲመርጥ በማድረግ መራጩ ሕዝብ ሳይጉላላና ሳይጨናነቅ የሚመርጥበት ሁኔታ ተመቻችሏል፡፡

8. በእያንዳንዱ 43000 የምርጫ ጣቢያ ከሕዝብ የተመረጡና የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ላለመሆናቸው የተረጋገጡ 220,000 የሕዝብ ታዛቢዎች ተመድበዋል፡፡

9. ከአስር በላይ የሲቭክ ማኀበራት ያቋቋሙት የሲቪክ ማኀበራት ጥምረት ከ42000 ታዛቢዎች በላይ / በአማካይ አንድ ሰው በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ / ተመድበው ታዝበዋል፡፡

10. ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሚወዳደሩበት እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ታዛቢዎች እንዲመደቡ የምርጫ ሕጉ የፈቀደላቸው ሲሆን በአውሮፓ ሕብረት ታዛቢዎች ሪፖርት መሰረት በ90%ቱ ጣቢያዎች ታዛቢዎቻቸውን ልከዋል፡፡

11. የአፍሪካ ህብረት 60 ታዞቢዎች፣ የአውሮፓ ህብረት 160 ታዛቢዎች አሰማርተው ምርጫውን ታዝበዋል፡፡ የውጭ ታዛቢዎች በተለይ ቁልፍ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎች በሚወዳደሩባቸው የምርጫ ክልሎች የምርጫ ሂደቱን፣ ምርጫውንና ቆጠራውን በቅርበት ተከታትለዋል፡፡

ምርጫው በዚህ አመቺ ሁኔታ ነበር የተካሄደው አንድ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች አመቺ ሁኔታ ከመፍጠር ውጭ ሕዝቡን ተክቶ አንዱን ወይም ሌላውን ፓርቲ የማስመረጥ መብት የለውም፡፡ በዚህ ሁኔታ ተቃዋሚዎች በዜሮ የተሸኙበት ምክንያት ምንድን ነው ?

## ለ. <u>የተገኘው ውጤት ምክንያቶች</u>

### *I. <u>የኢህአዴግ ጥንካሬ</u>*

1. የኢህአዴግ መንግሥት ለተከታታይ ስድስት ዓመታት ኢካኖሚውን ከ11% በላይ ማሳደጉ ሕዝቡ የልማት ጥቅምን ማጣጣም እንዲጀምርና የልማት ጥቅም ያልደረሰውም ቢሆን የልማት ተስፋ እንዲያሳድር ማድረጉ ለአሸናፊነቱ ዋናው ምክንያት ነው፡፡ በታሪክ በዚህ ፍጥነት ልማት ያመጣ ፓርቲ የተሸነፈበት ሁኔታ አይታወቅም፡፡

2. ድርጅቱ በየደረጃው የነበሩትን የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመፍታት ያደረገው ጥረት አስከታች የመስተዳድር አካላት የተሳካለት ባይሆንም በከፍተኛ አመራር የታየው የለውጥ ቁርጠኝነት ድጋፍን አስገኝቶለታል፡፡

3. ድርጅቱ ባለፉት ዓመታት የውስጥ ድርጅታዊ አሰራሩን በማሻሻልና ቀደም ሲል የነበሩትን ችግሮችን በሕዝብ አስተያየት ላይ ተመስርቶ በመቅረፍ የተጠናከረ ድርጅታዊ አቋም ይዟል:: የአባልነት መሰረቱን በማስፋትም አባላቱን ከአምስት ሚሊዮን በላይ አድርሷል:: ይህ ድርጅታዊ ኃይል ለምርጫ ዘመቻው ጠንካራ መሳሪያ ሆኖታል::

4. ኢህአዴግ በምርጫ ክርክሩ ወቅት የተሻለ ዝግጅት የነበረው ብቻ ሳይሆን፣ የተሰጠው ነፃ የአየር ጊዜ አሟጦ በመጠቀምና ሕዝቡን በሞያው፣ በፆታው፣ በእድሜውና በተለያዩ የአደረጃጀት መልኩ በማግኘት መልእክቱን በተሻለ መልኩ አስተላልፏል::

- ኢህአዴግ በሁሉም መስክ ያከናወናቸውና ያስመዘገባቸው ውጤቶች እንዲሁም በቀጣይ ዓመታት ለመስራት ያቀዳቸውን ተግባራት በተሻለ መልክ ለሕዝብ ማስተዋወቅ መቻሉ በጠንካራ ጐን የሚጠቀሱ ናቸው::

## II. <u>*የተቃዋሚዎች ድክመት*</u>

- ከ97ቱ ምርጫ በኋላ በአንድ በኩል ኢህአደግ እየተጠናከረ ሲሄድ በሌላ በኩል ደግሞ ተቀዋሚዎች እየተዳከሙ እና እየተከፋፈሉ መጥተዋል:: የቅንጅት መከፋፈል ደግሞ ሕዝቡ በተቃዋሚዎች ፖለቲካ ተስፋ እንዲቆረጥ አድርጐታል:: የ1997ቱ ቅንጅት በስድስት ድርጅቶች ማለትም መኢአድ፣ ኢዴፓ፣ አንድነት፣ቅንጅት፣ ግንቦት 7፣ መርህ ይከበር አንድነት ተከፋፍሎ ተከታዮቹን አሳዝኖል::

- ከኢህአደግ ጋር የተወዳደሩት ተቃዋሚ ፖርቲዎች 63 እንደመሆናቸው ሕዝቡ አንድ ወጥ የተቃዋሚዎች ድምጽና አጀንዳ መስማት አልቻለም:: አብዛኛዎቹም ለአምስት አመታት ጠፍተው በምርጫ ዘመን ብቅ የሚሉ በመሆናቸው በድርጅቶቹ ሕዝባዊነትና አገር የመምራት ዝግጁነት ላይ ሕዝቡ ከፍተኛ ጥርጣሬ እንዲኖረው አድርጐታል:: ተቃዋሚዎች የአዲስ አበባ መራጭ የ40%ቱን አካባቢ ድምፅ ቢያገኙም ተሸናፊ የሆኑበትም ሚስጥር ተከፋፍለው ድምፃቸውን ስለበጣጠሱት ነው::

- የተለያዩ የፖለቲካ ኘሮግራም ያላቸው ድርጅቶች ኢህአዴግን ለመጣል ብቻ በአጭር ጊዜ ፍላጐት ላይ ተመስርተው የፈጠሩት ስብስብ አገርን የማስተዳደር ዝግጁነታቸው በተመለከተ በቂ ሕዝብ ሊያሳምን አልቻለም:: ከዚህ አኳያ በመድረክ ስር የተሰባሰቡት ድርጅቶች በአብነት መውሰድ ይቻላል:: የመድረክ አባል ድርጅቶች በመሬት ጉዳይና አንቀፅ 39 መሰሉን ቁልፍ ጉዳይ ላይ ስምምነት ሳይኖራቸው ከተመረጥን በኋላ ጉዳዮቹ በሕዝብ ሪፌረንደም ይወሰናል ማለታቸው ብዙ ሕዝብ ብጥብጥን በአዳር ማቆየት አድርጐ ወስዶታል::

በአጠቃላይ ውድድሩ በአደረጃጀት፣ በፕሮግራም ጥራት፣ በማስፈፀም ብቃትና በታማኝነት ሰፊ ልዩነት ባላቸው ድርጅቶች መካከል የተደረገ ውድድር በመሆኑ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ ሁኔታ የሌላ አገር ሕዝብም ቢሆን ውሳኔውንና ምርጫው ከዚህ የተለየ እንደማይሆን መገመት አያስቸግርም::

## *ሐ. <u>ከምርጫው ውጤት በኋላ የተቃዋሚዎች ምላሽ</u>*

- አብዛኛዎቹ የምርጫውን ውጤት ተቀብለው ለአሸናፊው ፓርቲ የእንኳን ደስ አለህ መግለጫ ልከዋል::

- በርካታዎቹ በምርጫው ሂደት አለ የሚሉት ችግር በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ሂደቱን ጀምረዋል::

- የተወሰኑት ደግሞ ምርጫው ይደገም የሚል አቋም ይዘዋል::

- ተቃዋሚዎች ያላቸው አቤቱታ ምርጫው ይደገም የሚለውን ጭምር በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ የማቅረብ መብት አላቸው::

- አንዳንድ ተቃዋሚ ፖርቲዎች እስከ ምርጫው ቀን በሂደቱ ደስተኞች ነን ብለው ከምርጫው በኋላ አቋማቸውን መቀየራቸው ለሽንፈታቸው ኃላፊነት ላለመውሰድ መሆኑ መሰመር ይገባዋል::

- የምርጫ ቦርድ በቅርቡ ለመኢአድና ለመድረክ በሰጠው ዝርዝር ምላሽ ያቀረቡዋቸው ቅሬታዎች መሰረት እንደሌላቸውና ምርጫውን ለመድገም የሚያስችል ተጨባጭ ምክንያት እንደሌለ ገልፆል፡፡

## መ. ከምርጫው በኋላ የአሸናፊው ፓርቲ አቋም

- አሸናፊው ፓርቲ አሸናፊነቱን በትህትና ተቀብሎ በቀጣዮቹ አምስት አመታት በተቃዋሚዎች ጋር አብረን እንስራ የሚለው ጥሪው የተቃዋሚዎች አስተያየቶች እንዲደመጡ ከመርዳቱም በተጨማሪ የመቻቻል የፖለቲካ ባህልንም ያዳብራል፡፡

- ምንም አይነት የውጭ ግፊት ሳይበግረው የሕዝቡን "ድምጼን አክብሩልኝ " ጥሪ በፅናት ማክበሩ ትክክለኛ አቋም ነው፡፡

## ሠ. የአገር ውስጥና የውጭ ታዛቢዎች አስተያየቶች

- የአገር ውስጥ በሕዝብ የተመረጡ ታዛቢዎችና የሲቪክ ማኀበራት ጥምረት ታዛቢዎች ምርጫው ሰላማዊ፣ ነፃ፣ ፍትሃዊና ውጤቱ የሕዝቡን ፍላጐት የሚያንፀባርቅ መሆኑን መስክረዋል፡፡

- የአፍሪካ ሕብረት በተመሳሳይ መልኩ የምርጫው ሰላማዊ፣ ነፃ፣ ፍትሃዊ መሆን መስክረዋል፡፡ ይህም ሆኖ የአለም ሚድያዎች በነዚህ አፍሪካዊ የምስክርነት ቃሎች ላይ ምንም አይነት ዘገባ አላቀረቡም፡፡

- የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ሂደቱ ሰላማዊነትና የሕዝቡ ፍላጐት የተንፀባረቀበት መሆኑን እና የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ በሁሉም መስፈርቶች መያዊ የሆነ፣ በአግባቡ የተደራጀና ምርጫውን በተገቢው የመራ መሆኑን ቢገልፅም ከምርጫው ቀን ሁኔታ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ጉዳዮች በማንሳት ምርጫው ዓለም አቀፍ መርሆዎችን አያሟላም ብሏል፡፡ የፖለቲካ ምህዳሩ ለገዥው ፓርቲ የተመቸ ነበር የሚለው አቋም ቀደም ብሎ ከድርጅቱና

ከሌሎች የምዕራባውያን መንግሥታት ጋር መንግሥት የተለየ አቋም ነበረው ልዩነቱ ወደፊትም ይቀጥላል። ይህም ሆኖ የአውሮፓ ሕብረት የውጭ ግንኙነት ኃላፊ ለኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ለተካሄደው የተሳካ ምርጫ እንኳን ደስ አላችሁ ማለታቸው ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ሕብረት ጋር የሚኖራት ግንኙነት የበለጠ እንደሚጠናከር አመላካች ነው።